# <u>ተቃዋሚዎችን ከእስር የመልቀቁ እርምጃና አንድምታው</u>

**ኢዛና ዘመንፈስ 01-25-18**

ጠቅላይ ሚኒስቴር ሃ/ማርያም ደሳለኝ ታህሳስ 25 ቀን 2010ዓ/ም ከሌሎቹ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ሊቃነ መናብርት ጋር ለመገናኛ ብዙሃን በሰጡት ወቅታዊ ቃለ ምልልስ ላይ ”በፈፀሙት ወንጀል ምክንያት በፍርድ ቤት የተፈረደባቸው ወይም ደግሞ ወንጀል በመፈፀም ድርጊት ተጠርጥረው በአቃቢ ህግ ጉዳያቸው ተይዞ በእስር የሚገኙ አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲ አባላትን ጨምሮ ሌሎች ግለሰቦች የተሻለ ሃገራዊ መግባባት ለመፍጠርና የዲሞክራሲ ምህዳሩን ለማስፋት በማሰብ ክሳቸው ተቋርጦ ወይም በምህረት ህግና ህገመንግሥቱ በሚፈቅደው መልኩ ተገቢው ማጣራት ተደርጎ እንዲፈቱ ይደረጋል ›› የሚል ሃሳብ ሰንዝረው እንደነበር የሚታወስ ጉዳይ ነው፡፡ እናም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የተቃውሞው ጎራ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ጎላ ባለ መልኩ ሲነሳ የሚደመጠው አነጋጋሪ ርዕሰ ጉዳይ ‹‹ኢህአዴግ መራሹ መንግስት ኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ እስረኛ የለም ይል እንዳልነበር ይሄው አሁን ላይ ደግሞ ራሱው የፖለቲካ እስረኞችን እፈታለሁ ማለት ጀምሯል፡፡ ጉድ እኮ ነው ጎበዝ! እነዚህ ሰዎች ህዝቡ ይታዘበናል እንኳን አይሉም እንዴ!?›› የሚል ዓይነት ሆኖ እንዳገኘሁት ለመግለፅ እወዳለሁ፡፡

ስለዚህ እኔ በዛሬዋ መጣጥፌ ላነሳ የፈለኩትም፤ እውን የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር አቶ ሃ/ማርያም ደሳለኝ ታህሳስ 25ቀን 2010ዓ/ም የዕቅዱን መኖር ለህዝብ በገለፁበት ቃለ ምልልስ ላይ ‹‹የፖለቲካ እስረኞችን እንፈታለን›› ሲሉ ተደምጠዋልን? ወይስ ደግሞ ‹‹የተሻለ ሀገራዊ መግባባትን ለመፍጠር ይረዳል በሚል እምነት በራሳቸው ጥፋት ምክንያትም ቢሆን ለእስር የተዳረጉ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችንና አባላትን ክሱ እንዲቋረጥላቸው የማድረግ ውሳኔ ላይ ደርሰናል›› የሚለው አማርኛ ለኔ እንደሚገባኝ አይደለም ይሆን ትክክለኛ ትርጉሙ? ወዘተ በሚሉ ጥያቄዎች ዙሪያ የሚያጠነጥን ርዕሰ ጉዳይ ነው፡፡ እንግዲያውስ አሁን በቀጥታ ወደ ዋናው የፅሁፌ ዓላማ አልፌ መንግስት ያላለውን ያለ ለማስመሰል ሲባል ብቻ ጉዳዩን በተንሸዋረረ መልኩ ተርጉመውና አፋልሰው ሊያቀርቡት ሲሞክሩ የሚስተዋሉበትን የተቃውሞው ጎራ ፖለቲከኞች የተለመደ ፀጉር ስንጠቃ አነሳለሁ፡፡ (ስለሆነም ይህን መሰረተ ሃሳብ መነሻ አድርገን እውነቱን እንነጋገር ከተባለ ተቃዋሚዎች ለዓድዋው በኢትዮ ጣልያን መንግስታት የጦርነት ውሎ እንደ ዋነኛ መንስኤ ተደርጎ የሚወሰደውን የውጫሌ ውል አስራ ሰባተኛ አንቀፅ እንድናስታውስ የሚያስገድድ ማምታታትን ይሆነን ብለው የያዙት ይመስላሉ፡፡ ደግነቱ ግን

እንደዚህ ያለው ቀናውን ሃሳብ ሆነ ብሎ በማጣመም ያልተገባ ፖለቲካዊ ትርፍን ለማግኘት የመሻት ደባ እውነታውን የመቀየር ብቃት እንደማይኖረው የውጫሌ 17ቱ መዘዝ እንዳስከተለው ተደጋግሞ በተነገረለት የዓድዋው ጦርነት የድል ገድል ውሎ ላይ መረጋገጡን ታሪክ ዘግቦታል፡፡

ስለዚህም ከላይ ለአብነት ያህል ቀንጭበን የጠቀስነውን ሰሞነኛ መንግስትን የሚያጥላላ አስተያየት ሲሰነዝሩ የሚደመጡት ተቃዋሚ ፖለቲከኞች፣ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ የተናገሩትን በትክክል ካለመረዳት የሚመነጭ አይደለም ችግራቸው፡፡ ይልቅስ የኢፌዴሪ መንግስት ለምልዓተ ህዝቡ ያስተላለፈውን መሰረታዊ ቁም ነገር ለመረዳት ፍላጎቱ ስለሌላቸው እንጂ፡፡ እናም ከዚህ አብዛኛዎቹ የሀገራችን ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከትናንት እስከ ዛሬ ከሚታወቁበት የኢህአዴግ መራሹን መንግስት በጎ ጥረት ሁሉ ጥላሸት ለመቀባት ያለመ መሰል እብለት አኳያ ሲታይ፣ እውን ጠቅላይ ሚኒስቴራችን እንዳሉት በፈፀሙት የወንጀል ተግባር ምክንያት በሕግ ቁጥጥር ስር ውለው ክስ የተመሰረተባቸውን የተቃውሞው ጎራ ፖለቲከኞች እንዲለቀቁ ማድረግ ለተሻለ ብሔራዊ መግባባት መፈጠር ይበጃልን? የሚል ስጋት አዘል ጥያቄ እናነሳ ዘንድ ይገፋፋል፡፡ ምንም እንኳ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በተቃውሞው ጎራ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ምክንያት ሕግ ጥሶና ወንጀል ፈፅሞ ለእስር ከሚዳረግ ይልቅ፣ በእውነተኛ የሰላማዊ ትግል ሂደት የሚመጣ ለውጥን ሊመርጥ እንደሚገባ የማምን ሰው ብሆንም፣ ግን ደግሞ ይህ ዓይነቱ የአንድ ወገን ቅን አስተሳሰብ ብቻውን የሚጠበቀውን ውጤት እንደማያመጣ የከዚህ ቀደሙ ተሞክሯችን እንደሚያመለክት አለመዘንጋት ጠቃሚ ይመስለኛል፡፡

ለማንኛውም ግን የኢፌዴሪ መንግስት እያለ ያለው ፣ ተቃዋሚዎቹ ግለሰቦች በሕግ ቁጥጥር ስር ውለው ክስ የተመሰረተባቸው እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሊያስጠይቃቸው የሚችል የወንጀል ድርጊት ሲፈፅሙና ሲያስፈፅሙ በመገኘታቸው እንጂ የፖለቲካ አቋማቸው ግምት ውስጥ እየገባ አይደለም፡፡ እንዲህም ሆኖ ግን እስቲ እኛ ሆድ እናስፋና ተለቀው በሰላማዊ ትግሉ ሂደት ውስጥ የየራሳቸውን ገንቢ አስተዋፅኦ ማበርከት ይችሉ እንደሁ እንያቸው ነው፡፡ ስለዚህም ህዝቡ ጉዳዩን ከዚህ አኳያ ሊረዳው ይገባል የሚል እምነት ነው ያለኝ እኔ በግሌ፡፡

ምክንያቱም ደግሞ እነዚሁ ወገኖች ገና ከአሁኑ ምንም ዓይነት በሕግ የሚያስጠይቅ የወንጀል ድርጊት ሳይፈፅሙ ለእስር የመዳረግ ዕጣ የገጠማቸው በስልጣን ላይ ያለውን ገዢ ፓርቲ የሚያስፈራ አቋም የሚያራምዱ ጠንካራ ተቃዋሚዎች ስለሆኑ እንደሆነ አድርገው መናገርና ማስነገር የጀመሩበት አግባብ መኖሩን የሚያመለክቱ መረጃዎችን እየሰማን ያለንበት ሁኔታ አለና ነው፡፡ ለምሳሌ ያህልም

ባለፈው ጥር ሁለት ቀን 2010ዓ/ም ታትሞ የወጣው ሰንደቅ ጋዜጣ ላይ ጉዳዩን አስመልክተው ወቅታዊ ማብራሪያ እንዲሰጡ.ት ከተደረጉት የተቃውሞው ጎራ ፖለቲካ ልሂቃን አንደበት ስለተሰነዘረው አስተያየት አንስተን ብናስታውስ ‹‹ኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ እስረኛ የለም ማለት ፀሐይ በምስራቅ ወጥታ በምዕራብ ትጠልቃለች የሚለውን ዓለም አቀፋዊ እውነት እንደ መካድ ይቆጠራል›› የሚል ይገኝበታል፡፡ ይህን ያሉት የሰማያዊ ፓርቲ ፕሬዚዳንት አቶ የሺዋስ አሰፋ እንደሆኑም ማስታወስ ይቻላል፡፡ እናም እንደኔ እንደኔ የተሻለ ሀገራዊ የጋራ መግባባትን ለመፍጠር የሚረዳ ማንኛውም ዓይነት መካረሮችን የሚያለዝብ እርምጃ ሲወሰድ ማየት መለመድ የሚገባው መልካም ነገር የመሆኑን ያህል፤ ይህ በጎ ሃሳብ በሁሉም ወገኖች ዘንድ ተገቢ ዋጋ ሳይሰጠው እየቀረ ተቃራኒ ድምር ውጤት የሚያመጣበት አጋጣሚ ጥቂት አለመሆኑን መዘንጋት እንደማይኖርብን ግን ይሰማኛል፡፡

ይልቁንም ደግሞ ይህ አሁን የምንገኝበት ዘመን በኢትዮጵያውያን ህዝቦች ፖለቲካዊ የጋራ ታሪክ ውስጥ ፈፅሞ የተለየ ስፍራ ሊሰጠው እንደሚችል የሚመንበትን የአክራሪ ዲያስፖራ ተቃዋሚዎች ከለየለት የትምክህትና የጠባብ ብሔርተኝነት ፖለቲካዊ አስተሳሰባቸውን በተጠና ቅንብር የሚያዛምቱበት አግባብ የዚህችን ሀገር ፈተና በማወሳሰብ ረገድ እያሳደረ ስላለው ፈርጀ ብዙ አሉታዊ ተፅእኖ ሲታከልበት ጉዳዩን እጅግ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ያደርገዋል፡፡ እናም ኢትዮጵያውያን የብሔር ብሔረሰብ ህዝቦች የምንታወቅበት የጋራ ህልውናችን ለተመሰረተባት እናት ሀገር ዘለቄታዊ ዕጣፈንታ ይበጃል ከሚል ቀና አስተሳሰብ በሚመነጭ እምነት የሚወሰዱ መሰል እርጃዎችን ሁሉም ወገን ተገቢ ዋጋ እንዲሰጣቸው ማድረግ ያስፈልጋል እላለሁ፡፡

አለበለዚያ ግን ከዚህ ቀደም እስኪሰለቸን ድረስ ደጋግመን የታዘብነውን በኢህአዴግ መራሹ መንግስትና በፅንፈኛ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርዎች መካከል የሚደረግ የአመለካከት ገመድ ጉተታ (መቋጫ የለሽ ልፊያ) ከማስቀጠል የዘለለ ተጨባጭ ውጤት ይመጣል ብሎ ማመን ያዳግታል፡፡ ይህን የምልበት ዋነኛ ምክንያትም ከላይ ለማመልከት እንደሞከርኩት ሁሉ፤ ሌላው ቀርቶ መንግስት ለዚህች ሀገር ህዝቦች ዘለቄታዊ የጋራ ዕጣንታ መቃናት ይበጅ ይሆናል በሚል ተስፋ ስላቀዳቸው የእርምት እርምጃዎችና የመፍትሔ ፍለጋ ቀጣይ ጥረቶች የሚሰጠውን ማብራሪያ፤ ልክ እንደ የውጫሌው ውል 17ኛ አንቀፅ ለእነርሱ ዓለም አቀፋዊ ጥቅም መረጋገጥ እንዲያመች አድርገው እያንሸዋረሩ በመተርጎም ሌላ አላስፈላጊ ኪሳራ የሚያስከትል የቃላት ጦርነትን ሲከፍቱ የሚስተዋሉ ተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖች ጥቂት እንዳልሆኑ የሚካድ ጉዳይ አይደለም፡፡

ስለዚህም፤ ትርጉም ያለው ሀገራዊ የጋራ መግባባትን ለመፍጠር የሚያስችሉ መሰል እርምጃዎችን መውሰድ ይገባል የሚለው የኢፌዴሪ መንግስት አቋም ጠቃሚነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ታዲያ ይህ ጠቃሚ ዕቅድ ወደተጨባጭ ተግባር ተለውጦ ሀገራዊ ተስፋዎቻችንን እንዲያለመልምልን ከነማን ምን ቀሪ የቤት ስራ መስራት ይጠበቃል? ብሎ መጠየቅ ፈፅሞ ችላ መባል አይኖርበትም፡፡ መቸስ ‹‹ዓይን አይቶ ልብ ይፈርዳል›› የሚለውን የአበው ብሒል መነሻ አድርገን እቅጩን መነጋገር ካለብን፤ የሀገራችን ፖለቲካና ፖለቲከኞች መሰረታዊ ችግር ለዘመናት ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣው መሳፍታዊ መታበይ በሚመነጭ ቅንነት ማጣት ምክንያት ዕርስ በርስ መጠላለፍን እንደ ጠቃሚ ሙያ የሙጥኝ ማለት ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡ እናም ይሄው አብሮ ማደግ የሚቻልበትን ሀገራዊ ድል ለሚያቀዳጅ የጋራ ትንሳኤ መሳካት ከመረባረብ ይልቅ፤ ዕርስ በርስ እየተጠላለፉ ተያይዞ የመውደቅ አደጋን ለሚያስከትል ፍጥጫ የመመቻቸት አባዜ በከፋ መልኩ እንደተጠናወተን አምኖ መቀበልን የሚጠይቅ ከልብ የመነጨ ፖለቲካዊ ንስሐ የመግባቱ ጉዳይ ሁሉን አቀፍ እስካልሆነ ከተለመደው አጉል መቋሰል የምንላቀቅበት ይሆናል ወይ? የሚለው ጥያቄ ስር ነቀል ምላሽ የሚያሻው ቁልፍ ነጥብ ይመስለኛል፡፡ ሀገራዊ ወይም ደግሞ ብሔራዊ የጋራ መግባባት በተሻለ መልኩ ተፈጥሮ የማየት ምኞታችን እውን ይሆን ዘንድ ሁሉም የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ ችግር የመፍታት ጉዳይ ይመለከተኛል ብለው የሚያምኑ ወገኖች፤ ስለጉዳዩ አስፈላጊነት የምር እንደሚያምኑ የሚያረጋግጥ የየራሳቸውን ተግባራዊ እርምጃ መውሰድ እንደሚጠበቅባቸው ለመረዳት የተለየ ዕውቀት የሚጠይቅ አይደለም፡፡ እያንዳንዳችን የየራሳችንን መስቀል እየተሸከምን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ዳገትን ለመውጣት ተጨባጭ ድፍረት ማሳየት ስንችል ብቻ ነው ክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴሩ የተመኙትን የተሻለ ሀገራዊ መግባባት ማስፈን የሚቻለው፡፡ ስለዚህም አሁን የኢፌዴሪ መንግስት የሰጠውን ክስ የማቋረጥና ፍርድ የመሰረዝ ዕድል ተጠቅመው ከእስር እየተለቀቁ ያሉት ተቃዋሚ ፓለቲከኖች ሁሉ፣ ቢያንስ ከእንግዲህ ተመሳሳይ ሕገ ወጥ ተግባር ላይ እንደማይሳተፉ ሊያረጋግጡልን ይገባል እላለሁ፡፡